# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

### የእህቶች ፕሮግራም

የቤተ ክርስቲናችን የእህቶች አገልግሎት በNovember 9 ከ 3 p.m. እስከ 5 p.m. የቃል፣ የጸሎትና የህብረት ጊዜ ፕሮግራም ለህቶች ሁሉ መዘጋጀቱን በደስታ ይገልጻል። ቦታው በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ይሆናል። እህቶች ሁሉ ተጋብዛችኋል። ወንድሞች እህቶች እንዲካፈሉ እንድታበረታቱ አገልግሎቱ ያሳስባል።

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

### የልጆች አግልግሎት ቀን

በOctober 27 በሚኖረው የሕሁድ አገልግሎት ልጆቻችን አዋቂዎችን የሚያገለግሉበት እለት ነው። በዚህ እለት ስለሚኖረው ፕሮግራም እየጸለይን እንድንቆይ እናሳስባለን። የተለየ ግሩም ግዜ ስለሚኖረን በዚህ ፕሮግራም ሁላችንም እንድንካፍለ እናበረታታለን።

### እርስ በርስ እንተያይ

የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፦ ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፦ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ **የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?**
- ⇒ **በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?**
- ⇒ **ማገልገል ይፈልጋሉ?**
- ⇒ **Yeec.org App ጭነዋል?**
- ⇒ **http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?**

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፦**
**773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)**
**773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)**
**630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)**
**773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)**
**773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)**

**<u>መደበኛ ፕሮግራሞች</u>**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2:10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




## "... የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል..."

(2ቆሮ. 5:14)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**October 20, 2019** | **ጥቅምት 9፣ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

**ጸሎት ............................** ወንድም ረድኤቱ ካሳ

**አምልኮ..........................** የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

**ፕሮግራም መሪ .............** እህት ሰናይት ከበደ

**ቃል ...............................** ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ

**ማጠቃለያ .......................** ፕሮግራም መሪ

## የሳምንቱ ጥቅስ

“በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር
በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።”
(ሮሜ 5:5)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ፍቅር።

የእግዚአብሔር ፍቅር በልባቸን የፈሰሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው። በሮሜ 5:5 ላይ የእግዚአብሔር ቃል “በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም” ይለናል። “ፈሰሰ” የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ፍቅር ያለገደብ ወደ እኛ እንደመጣ የሚገለጽ ነው። ለኛ የተገለጠው የእግዚአብሔር ፍቅር ወደር የለውም። የዚህን ፍቅር ጥልቀት ለመግለጽ ሐዋሪያው ጳውሎስ “ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል” (ሮሜ 5:8) ይለናል። የእግዚአብሔር ፍቅር በኛ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ አይደለም። ልጁን ለኛ እንዲሞት የፈቀደው እኛ ገና በሐጢያት ሳለን እና ፈጽሞ የማይገባን ሆነን ነው። የዚህ ፍቅር ምንጭ እግዚአብሔር እራሱ ነው። እግዚአብሄር ከርሱ በወጣው ፍቅር ወዶናል። ዛሬም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም እግዚአብሔር ይወደናል። የኛ መንፈሳዊ መረዳት እና የሕይወት ምልልስ እግዚአብሔር ለኛ ያለውን የፍቅር ደረጃ አይወስንም። ይህ ፍቅር ለሰው ልጅ ሁሉ የተገለጠ ነው። ክርስቶስ ለአለም ሁሉ (ለሰው ዘር ሁሉ) ነው የሞተው። የኛ ድርሻ ወደ እግዚአብሔር የፍቅር ጥሪ በመታዘዝ መግባት ነው።

እግዚአብሔር ስለወደደን ተስፋን ሰጥቶናል። ይህ ተስፋ ደግሞ ይሚያሳፍር ተስፋ አይደለም። የሚፈጸመም፤ የሚሆን ተስፋ ነው። ለዚህ ደግሞ ያለን ዋስትና የእግዚአብሔር ፍቅር ነው። እግዚአብሔር አንድ ልጁን በመስጠንት ለኛ ያለውን ፍቅር ያውም እኛ ገና ኃጢያተኞች ሳለን ስለገለጸ የሰጠንን ተስፋ ሁሉ እንደሚፈጽምልን እርግጠኞች ነን። በእርግጥ ቃሉ እንደሚያስተምረን “ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?” (ሮሜ 8፡ 32) በእርግጥ ልጁን የሰጠን ጌታ ከልጁ ጋር ሁሉን እንደሚሰጠን እናምናለን።

ለኛ የተገለጠው የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመረዳት የሚንችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን “ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ” እጸልያለሁ ይላል። ፍቅሩ ጥልቅ ነው። የመጨረሻ አዘዕቅት ውስጥ ያለነውን ይደርሳል። ከፍታው እስከ ሰማየ ሰማያት ይደርሳል። ለሁሉም የሚበቃ ሁሉንም ለማቀፍ የሚችል ነው ስፋቱ። የክርስቶስን ፍቅር በአእምሮአችን ተረድተን የሚንጨርሰው አይደለም። ከአእምሮ በላይ የሆነ ነውና ከመታወቅ ያልፋል። የክርስቶስን ፍቅር እናውቀው ዘንድ ኃይልን የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ይህ ፍቅር በልባችን ፈሶ እንዳለ ያሳውቀናል። በዚህ ፍቅር ውስጥም ለመመላለስ እንድችል አቅም ይሰጠናል።

የእግዚአብሔርን ፍቅር ስንረዳ ለተጠራንበት መጠራት እንደሚገባ እንድንኖር ኃይል እናገኛለን። እግዚአብሔርንም ለማገልገል ኃይል እናገኛለን። ስለዚህ ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ “የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናል” የሚለን። (2ቆሮ. 5:14) ፍቅሩን ከተረዳን የሚያቆመን ምንም ነገር አይኖርም። ለዚህ ነው ጌታ ኢየሱስ ከፍቅሩ ተነስተን እንድናገለግለው ያስተማረን። ከወደድነው ራሳችንን ቅዱስ መስዋዕት አድርገን እናቀርብለታለን፣ በትጋትና በግለት እናገለግለዋለን፣ እርሱ የወደዳቸውን እንወዳለን። ወገኖቼ፡- መንፈስ ቅዱስ ለኛ የተገለጠውን የክርስቶስን ፍቅር ተረድተን በፍቅሩ እንድኖርና እንድንመላለስ ኃይልን ይሰጠናል። አሜን!